# Doctrinal Theology
## የኢትዮጵያ ኦርቶዶስክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መርሆዎች

### የመጽሐፉ ይዘት በአጭሩ ሲተነተን

ይህ የሥነ-መለኮት መጽሐፍ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶስክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በእጅጉ ይጠቅማል ተብሎ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከሌሎች መጻሕፍት ልዩ የሚያደርጉት በርከት ያሉ ባሕርያት አሉት። ከእነዚህም ልዩ ባሕርያት አንዱ መጽሐፉ በይዘቱ ሰፊና ከሞላ ጎደል ሁሉንም የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምሕሮዎች በአንድ ላይ ያጠቃለለ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በአቀራረቡ አነጻጻሪና በተለይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ መልስ ያልተገኘላቸውን አጨቃጫቂ ትምህርቶችን በሰፊው እያብራራ ከኦርቶዶክስ አስተምሕሮ አንጻር ትክክለኛውን መልስ የሚሰጥ መሆኑ ነው።

መጽሐፉ በአሥራ አንድ ምዕራፎች ተከፋፍሏል። የእያንዳንዱ ምዕራፍ ርዝመት በውስጡ እንደ ተካተተው የትምህርት ይዘት ይለያያል።

1) የመጀመሪያው ምዕራፍ በዘመናችን የእግዚአብሔርን ሕልውና ለሚክዱ ሰዎች ምክንያታዊ በሆነ መንገድ እያብራራ በሥነ-መለኮታዊ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ አጥጋቢ መልስ ይሰጣል።
2) ሁለተኛው ምዕራፍ ሥነ-ፍጥረትን በአጭሩ ይዳስሳል። በዚህም ውስጥ ሰባቱ ሰማያት፣ ሰማይና ምድር (አራቱ ባሕርያት)፣ ረቂቃን ፍጥረታት ቅዱሳን መላእክት እንዲሁም የሰው ልጅ ልዩ አፈጣጠርና ሰብአዊ ባሕርይው በዘርዝር ተካተዋል። ከእነዚህ መካከል የረቂቃን መላእክት ተፈጥሮ፣ አገልግሎታቸውና አሰላለፋቸው የኦርቶዶክስን አስተምሕሮ በጠበቀ መልኩ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ በመሆኑ አብዛኛውን የምዕራፍ ክፍል ይሸፍናል።
3) ምዕራፍ ሦስት የሥላሴን አድነት ሦስትነት ይዳስሳል። መጽሐፉ የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ትምህርት በመላው የኦርቶዶስና እንዲሁም በአንዳንድ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተመሳሳይነት እንዳለው ያመለክታል። የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የሚያዛባ "ፊሎኬ" የተባለ አዲስ አስተምሕሮ በመጨመሯ በዚህ ረገድ ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የተለየች መሆኗን ያመለክታል።
4) በምዕራፍ አራት የተካተተው የክርስቶስ ትምህርት ነው። ጸሐፊው በዚህ ክፍል የምዕራባዊያንን የተዛባ ዘገባ በማረም የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ክፍፍል እውነተኛ ምክንያቱ ምን እንደነበር በትክክል ያስቀምጣል። ከዚህም ጋር "ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ" በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ኦርቶዶክሳዊያንና ካቶሊካዊያን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብለው በጋራ የሚቀበሏቸው ቀደምት ሊቃውንት ያስተማሯትና ከቤተ ክርስቲያን ክፍፍል በፊት የነበረች ቀጥተኛ አስተምሕሮ መሆኗን በጽሑፉ ያረጋግጣል።
5) ከምዕራፍ 5-10 ባለው ክፍል እንደ ቅደም ተከተላቸው የሚከተሉት ትህምርቶች ተጠቃለዋል።
   - የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትርጉምና ማንነት፣
   - የቅድስት ድንግል ማርያም ክብርና በሰው ልጆች የድኅነት ታሪክ ውስጥ ያላት ቦታ፣
   - የጻድቃንና የቅዱሳን መላእክት ክብርና የአማላጅነትና ጸጋ፣
   - ኦርቶዶክሳዊ የአምልኮት ሥርዓት በተለይም የቅዱሳን ስዕላት ክብርና የዕጣን አገልግሎት፣
   - የድኅነት ትርጉምና ድኅነት የሚገኝባቸው ቀጥተኛ መንገዶች፣ እንዲሁም
   - የሰባቱ ምሥጢራት አገልግሎትና በሰው ልጆች ድኅነት ያላቸው ቦታ።

በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያሉትን የአስተምሕሮ ልዩነቶች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጎ እያነጻጸሩ ማቅረብ የአንባቢን ልብ ይማርካል። ለሕሊናም ያረካል። በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሠረተን ትምህርትና የአምልኮ ሥርዓት አንተ ስለጠላኸው ብቻ መንቀፍ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለውን ትምህርትና ሥርዓት ስለወደድከው ብቻ ትክክለኛ ለማስመሰል መሞከር አንተን ከሕሊና ወቀሳ ነጻ አያደርግህም፤ የቤተ ክርስቲያንህንም እውነተኛነት አያረጋግጥም። ለምሳሌ ምንም እንኳን ቅዱስ መጽሐፍ በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ ማብራሪያ የሚሰጥ ቢሆንም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የራሳቸውን መንገድ ብቻ ስለሚከተሉ **"ሰው እንዴት መዳን ይችላል"** በሚለው ቁልፍ የክርስትና ትምህርት ላይ ከኦርቶዶክስ ይለያሉ። እውነትን እንከተል ከተባለ ሁሉም የክርስትና ትምህርቶች በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተመሠረቱና በሃያማኖት አባቶች ማለትም በቅዱሳን ሐዋርያትና በተከታዮቻቸው ምስክርነት የተሰጠባቸው ሊሆኑ ይገባል። ለምሳሌ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ እንደ አምልኮ ጣኦት የሚቆጠሩት የቅዱሳን ስዕሎች ክብርና የዕጣን አገልግሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡና በቅዱሳን አባቶች አስተምሕሮ የተረጋገጡ እውነታዎች ናቸው። እነዚህና ሌሎችም ኦርቶዶስካዊ ሥርዓቶች በምዕራፍ 8 በሰፊው ተገልጸዋል። በዚህ መጽሐፍ ከተጠቀሱት አንጻጻሪ ትምህርቶች መካከል በኦርቶዶስክ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት የሌላቸውና አንዳንድ ጊዜም በስህተት ሲጠቀሱ የሚስተዋሉ "እሳት መንጽሔ" እና "ለድኅነት የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ" የተባሉ ሁለት የሮማን ካቶሊክ አስተምሕሮዎች በምዕራፍ 9 በሰፊው ተብራርተዋል።

11) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ሰፊ ሽፋን ከተሰጣቸው የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች መካከል በመጨረሻ በምዕራፍ 11 ላይ የቀረበው የዓለም ሕልፈትና ምልክቶቹ ናቸው። ምንም እንኳን የክርስቶስ ዳግም መምጣት ትንቢታዊና በመንፈሳዊ በመሆኑ አንደ ታሪክ ትምህርት በቅደም ተከተል በትክክል ማስቀመጥ ባይቻልም፣ መጽሐፍ ቅዱስን

መሠረት በማድረግ መልክ ለማስያዝ ተሞክሯል። ይህም ክፍል ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት አስቀድሞ የሚከሰቱ አስፈሪ የዓለም ምልክቶች፣ አውሬው ዳግም ከመከሰቱ በፊት መንገድ ጠራጊዎቹ ዓለምን ለማሳሳት የሚገለገሉበት የጥሪ ኮድ 666 እና ምንነቱ፣ ለአወሬው መንገድ የሚጠርጉ ሐሰተኛ ነቢያት በክርስትናው ዓለም ላይ የሚፈጥሩት ጫና፣ አውሬው ጊዜውን ጠብቆ ሐሳዌ-መሲህ በሚል ስም እንደገና በሥጋ ሲገለጽ በዓለም ላይ የሚከተለው ክህደትና ብሎም ዕልቂት፣ በመጨረሻም የሙታን መነሳት፣ የክርስቶስ መገለጥና በፍርድ ዙፋን መሰየም በጠቅላላ በመጨረሻው ምዕራፍ የሚተካተቱ ሐሳቦች ናቸው።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የዚህ መጽሐፍ ሁለት ልዩ ባሕርያት ተገላጊነቱን የጎላ ያደርጉታል።

1) መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ በመሆኑ በውጭው ዓለም ለሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በተለይም ለወጣቶችና ስለ ኢትዮጵያ ኦርዶዶስክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምሕሮ ሙሉ ግንዛቤ ማግኘት ለሚፈልጉ እንግሊዘኛ ተናጋሪዎች፣ እንዲሁም በሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ለሚገኙ ደቀ መዛሙርት እንደ መጀመሪያ የትምህርት መንጭ (ሪሶርስ) በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

2) በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተፈርተው የኖሩ ግልጽ መልስ ያልተሰጠባቸው ድብልቅና አጨቃጫቂ የትምህርት ርዕሶች በድፍረት የተካተቱበና ምልሻ ያገኙበት መጽሐፍ በመሆኑ ይህ በራሱ ብቸኛና ተፈላጊ ያደርገዋል።

ዘመኑ ከፈጠረው የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሲኖዶስ መከፈል ሌላ አሁን በአለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ልዩ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቃለች። በአንድ በኩል ለበዙ ዘመናት የኦርቶዶክስን አስተምሕሮ ለመቀየር ሲደክሙ ኖረው ያልተሳካላቸው ፕሮቴስታንቶች በቤተ ክርስቲያኒቱ በተፈጠረው የአስተዳደር ክፍተት ምክንያት ውስጥ ለመግባት ዕድል ያገኙበትና የመቀልበስ ሥራቸውን እያጣደፉ ያለበት ሁኔታ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምሕሮ እንከላከላለን የሚሉ ክፍሎች የሚወስዱት ጥበብና ማስተዋል የጎደለው እርምጃ እየፈጠረ ያለው ትርምስ ነው። ቀናኢነት አንድ ነገር ነው፤ አክራሪነት ደግሞ ሌላ ነው። መናፍቃንን ከቤተ ክርስቲያን የማስወጣት ርምጃ በጭፍን ሁከት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ትዕግስትንና መንፈሳዊነትን የተላበሰ ሊሆን ይገባል። አርዮስ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ ቀርቦ ተከራክሮ፣ እንዲመለስ ዕድል ተሰጥቶ ብሎም ተጸልዮለት ሊመለሰ ስላልፈለገ ነው እንደወጣ የቀረው እንጅ በሌለበት ተወግዞ ወይም በአድማ ተባሮ አልነበረም።

እነዚህ ክፍሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኦርቶዶክሳዊና ኦርቶዶክሳዊ ያልሆነውን አስተምሕሮ የሚለዩበት በቂ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ክህሎት ስለሌላቸው እንኳን የተቃውማቸውን መናፍቅ ነው ብለው የሚጠራጠሩትን ሁሉ በስሜት "ተሐድሶ" እያሉ ከቤተ ክርስቲያን ማስወጣትን እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጥሩታል። እነዚህ ክፍሎት ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ጠበቃ አድርገው ካቆሙ ወዲህ ትውልዱ መስመሩን ስቷል። እነሱን የሚከተለውም ሆነ እነሱን በእልህ የሚቃወመው ሁሉ የሞራል ዝቅጠት ውስጥ ወድቋል። በየትኛውም የክርስትና ዓለም የማይደረግ ጳጳሳትን መሳደብና በአንደባባይ ማዋረድ እየተለመደ መጥቷል። ጸሐፊያን አንደበታቸው ተሸብቧል፤ እጃቸው ታስሯል። በዚህ ዘመን በእምነት ላይ የተፈጠሩ የአስተምህሮ ልዩነቶችን በጭዋ ደንብ ለመፍታት ቁጭ ብሎ መነጋገር የሚታሰብ አይደለም። በዚህም ምክንያት ብዙ የቤተ ክርስትያን ልጆች የእመነት አቋማቸውን የሚገልጹበት ዕድል አጥተው በሌሉበት ተወግዘው ከቤተ ክርስቲያን ውጥተው ቀርተዋል። ብዙ ክርስቲያኖችን ተኩላ ነጥቋቸዋል፤ አውሬ በልቷቸዋል። ስለዚህ የጸሐፊው የእምነት አቋም እንዳለ ሆኖ ይህ መጽሐፍ ኦርቶዶክሳዊ የሆኑትንና እንዲሁም በኦቶዶክስ አስተምሕሮ ላይ በየዘመኑ ስርዋጽ የገቡትን ወይም ካቶሊካዊ ሆነው ኦርቶዶክስ መልክ ይዘው የቀሩትን አስተምሕሮዎች ቁልጭ አድርጎ በማሳየት በእምነተዎ ላይ የራሰዎን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ይረዳዎታል።

በአጠቃላይ 75 በመቶ የሚሆነው የመጽሐፉ ሐሳብ በእንግሊዝኛ ከመቅረቡ በቀር ተደጋግሞ ሲነገር የቆየ የቤተ ክርስቲያናችን አስትምሕሮ ሲሆን ቀሪው 30 በመቶ ደግሞ ከዚህ በፊት በሊቃውንት ያልተዳሰሱና በንጽጽር መልክ የቀረቡ አከራካሪ ነጥቦችን የያዘ ነው። መጽሐፉ በእንግሊዝኛ የተጻፈ እንደመሆኑ በአማርኛ ቋንቋ በትክክል ሊገለጹ የማይችሉ በርካታ የግሪክኛና የእብራይስጥ ቃላት ተካተውበታል። የእነዚህን ቃላት ትክክለኛ ፍች በውል ካልተረዳን እያነበብን ባለው ሐሳብ ላይ የሚኖረን ግንዛቤ የተዛባ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ነጥቦች ሲያጋጥሙ ጸሐፊውን ጠይቆ መረዳት ያስፈልጋል። ያም ሆኖ ግን በውጭው ዓለም በየትኛውም ደረጃ ላይ ያሉ ወጣቶች በቋንቋቸው የተጻፈውን ነገር በቀላሉ አንብቦ የመረዳት ክሂሎታቸው ከፍ ያለ በመሆኑ ልጅዎ ከዩኒቨርሲቲ ሲመረቅ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ሲያጠናቅቅ በሽልማት መልክ የሚሰጡት ትልቁ ውርስ ይህ መጽሐፍ ሊሆን እንደሚጋባ የመጽሐፉ አዘጋጅ ያምናል።

ሃይማኖታዊ መጽሐፍ የአእምሮ ጭማቂ የመንፈስ ፍሬ ነው። ይቅመሱት ያጣጥሙት፤ ራሰዎትን ያንጹ፤ መንፈሰዎትን ይገንቡ። የሃይማኖት መጽሐፍ ዘመን የማያስረጀው ለትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ ነው። ያንብቡት፤ ለልጅዎ ያውርሱት።

የእግዚአብሔር መንፈስ ዓይነ-ልቦናዎትን ያብራለዎች፤ አሜን።

መልካም ንባብ